የምዝገባ ቁጥር
Reg. No. 1146

የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ
HUMAN RIGHTS COUNCIL

ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው።
HRCO stands for democracy, the rule of law *and* the respect of human rights.

ሰመጉ
HRCO

ቀን፣ መጋቢት 3/2003 ዓ.ም

# የመንግስት የልማት እንቅስቃሴ የዜጎችን እድገት እና መሰረታዊ ፍላጎቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት እንጂ መብቶቻቸውን የሚያሳጣ መሆን የለበትም።

## 115ኛ ልዩ መግለጫ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) ማንኛውም አርሶ አደር ከመሬቱ እንደማይነቀል ያረጋግጣል። ከዚህ በተጨማሪ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ 456/1997 አንቀጽ 5(1)ሀ በግብርና የሚተዳደሩ አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነጻ እንዲያገኙ እንደሚደረጉ ይደነግጋል። እንዲሁም የዚሁ አዋጅም አንቀጽ 7(3) የገጠር መሬት ባለይዞታ ለሕዝብ ጥቅም መሬቱን እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ማሻሻያ እና ላፈራው ንብረት ተመጣጣኝ ካሳ ይከፈለዋል ወይም በለቀቀው መሬት ምትክ በተቻለ መጠን ሌላ ተለዋጭ መሬት እንዲያገኝ ይደረጋል ይላል። በመጨረሻም ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅም 455/1997 አንቀጽ 3(1) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አግባብ ያለው የመንግስት አካል የተሻለ ልማት ለማካሄድ ያስችላል ብሎ ያመነበትን የገጠር ወይም የከተማ መሬት በአዋጁ መሰረት ካሳ እንዲከፈል በማድረግ የማስለቀቅ ስልጣን አለው ይላል።

የኢፌዲሪ ህገመንግስት ስለ የአካባቢ ደህንነት መብት በሚደነግገው አንቀጽ 44(1) ሁሉም ሰዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው በማለት ይገልጻል። ይሁንና ከነዚህ ድንጋጌዎች በተቃራኒ በሚከተለው ሁኔታ የአርሶ አደሮች መብት ተጥሷል።

## የመብት ጥሰቱ መንስኤ

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን አዳ ወረዳ መንዱቤ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ከ 1967 ዓ.ም ጀምሮ የእርሻ መሬት ይዞታ ኖሮአቸው በግብርና ኑሮአቸውን ይገፉ የነበሩ አርሶ አደሮች ከ 1985 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በቢሾፍቱ ከተማ መስፋፋት ምክንያት የእርሻ

ይዞታቸው የነበረው መሬት ያለምንም ካሳ ክፍያ ተወስዶባቸው ለባለሀብት የተሰጠ ሲሆን በተጨማሪ በገበሬ ማህበሩ 'ጎልባ' ተብሎ በሚጠራው ቦታ የሚገኝ ቀሪ የእርሻ ይዞታቸው ላይ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ ክምችት ያለው የከተማ ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ መጣያ በመደረጉ የመንደሩ ነዋሪዎች ጤና በከፍተኛ ሁኔታ እየታወከ ሲሆን የቤት እንስሶቻቸው በሚበሉት ቆሻሻ ጤናቸው እየታወከ ከብቶች እየሞቱባቸው ይገኛሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረው አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸው ከሕግ አግባብ ውጭ ተወስዶባቸው ካሳ ወይም ተለዋጭ መሬትም ሳይሰጣቸው ከነቤተሰባቸው ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀዋል፡፡

በዚህ አይነት ህገወጥ ድርጊት ከ25 እስከ 38 አመት ድረስ ግብር እየከፈሉ ሲጠቀሙበት የቆዩትን የእርሻ መሬት ካሳ ወይም ተለዋጭ ቦታ ሳይሰጣቸው ተወስዶባቸው ለባለሀብት በመሰጠቱ ምክንያት በከፍተኛ ችግር ላይ የሚገኙ አርሶ አደሮች ስም ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፣

| ተ.ቁ | ስም | የግብር መጠን | የደረሰኝ ቁጥር | ለመጀመሪያ ጊዜ ግብር የከፈሉበት ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ለገሰ ገ/ጊዮርጊስ | 10 ብር | 54192 | 1976 |
| 2 | መምሬ መርሀዊ | 7 ብር | 97468 | 1970 |
| 3 | መምሬ ምክሩ | 10 ብር | 607975 | 1977 |
| 4 | አቶ ላቀው ገ/ወልድ | 10 ብር | 4881 | 1976 |
| 5 | አቶ ዘመዴ ኢርኮ | 10 ብር | 61308 | 1977 |
| 6 | አቶ በጋሻው ጎርፌ | 10 ብር | 678344 | 1978 |
| 7 | አቶ በየነ ደመቀ | 10 ብር | 601308 | 1977 |
| 8 | ወ/ሮ ዘነበች አበበ | 10 ብር | 4888 | 1976 |
| 9 | አቶ ደሳሉ ተሲላ | 10 ብር | 678190 | 1978 |
| 10 | አቶ ደምሴ በልዳ | 10 ብር | 601278 | 1977 |
| 11 | አቶ ማርእሸት ገ/ስላሴ | 10 ብር | 678329 | 1978 |
| 12 | አቶ ጣፋ አለሙ | 10 ብር | 54194 | 1976 |
| 13 | አቶ አቤቤ ራያ | 10 ብር | 678195 | 1978 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 14 | ወ/ሮ ድንቂ ራያ | 10 ብር | 678196 | 1966 |
| 15 | አቶ አለሙ በዳኔ | 10 ብር | 678175 | 1978 |
| 16 | ወ/ሮ ተስፋዬ እሸቱ | 10 ብር | 678238 | 1978 |
| 17 | አቶ ወርቂ ደግፌ | 10 ብር | 607985 | 1977 |
| 18 | ቀኝ አዝማች ብስራት እርገጤ | 10 ብር | 04885 | 1976 |
| 19 | ወ/ሮ ወለተወልድ ጩካ | 20 ብር | 26918 | 1972 |
| 20 | አቶ ጸጋዬ ወርቅነህ | 10 ብር | 608047 | 1978 |
| 21 | አቶ ማሞ መሩ | 10 ብር | 13349 | 1977 |
| 22 | አቶ ዘረፉ በሻህ | 10 ብር | 601312 | 1978 |
| 23 | አቶ በቀለ ግሩሙ | 10 ብር | 678192 | 1978 |
| 24 | አቶ አበራ ወ/ሚካኤል | 10 ብር | 601321 | 1976 |
| 25 | ወ/ሮ ማሚቱ ወልዳይ | 10 ብር | 678167 | 1977 |
| 26 | አቶ ፈይሳ ደጉ | 10 ብር | 678200 | 1976 |
| 27 | አቶ ኃ/ማርያም ኃ/ወልድ | 10 ብር | 84197 | 1978 |
| 28 | አቶ ጄሳ ኤሮ | 10 ብር | 601304 | 1978 |
| 29 | አቶ አሚ አድሬ | 10 ብር | 54243 | 1977 |
| 30 | አቶ አለሙ ገብሬ | 10 ብር | 678152 | 1978 |
| 31 | አቶ መብራቱ ባንጃው | 10 ብር | 678580 | 1978 |
| 32 | አቶ ጉዳ ጎበና | 10 ብር | 04877 | 1977 |
| 33 | ወ/ሮ እታለማሁ ሀይሉ | 7 ብር | 97486 | 1968 |
| 34 | አቶ ተ/ጊዮርጊስ ክልሌ | 10 ብር | 678240 | 1978 |
| 35 | አቶ ተፈራ ነጋሽ | - | - | - |

## <u>ማጠቃለያ፣</u>

የእርሻ መሬታቸውን ከህግ አግባብ ውጭ ያለ ካሳ ወይም ተለዋጭ መሬት ሳይሰጣቸው መብታቸውን ያጡት አርሶ አደሮች ብዛት የግብር ደረሰኛቸውን ለሰመጉ ያቀረቡት 35 ሲሆኑ ቁጥራቸው 44 እንደሆኑ የተለያዩ ሰነዶች ያሳያሉ ነገር ግን ቁጥራቸው ከዚህም እንደሚበልጥና 65 አባወራዎች እንደሆኑ ተወካዮቻቸው ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡ ለብዙ አመታት የመንግስትን የህግ ከለላና ድጋፍ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረትና ብዙ ድካም የጠየቀ ውጣ ውረድ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም በእርሻ መሬታቸው ላይ የተጣለው እና በመጣል ላይ ያለውን የከተማ ደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ በጤናቸው ላይ ከፍተኛ ችግር እያደረሰባቸው መሆኑን በመግለጽ አቤቱታቸውን በየደረጃው ለሚገኙ ለክልልና ለፌዴራል መንግስት አካላት አቅርበዋል ነገር ግን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሚሰጥ ምላሽ ባለማግኘታቸው አርሶ አደሮቹ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀዋል፡፡

መንግስት የአቤቱታ አቅራቢዎቹንና ብሎም በስራቸው የሚገኙ የቤተሰቦቻቸው አባላት ችግር የሚያስወግድ ምንም አይነት ህጋዊ እርምጃ አልወሰደም፡፡ ይህም መንግስት ዜጎችን በህግ አግባብ እንዲያስተዳድርና ደህንነታቸውን እንዲያስጠብቅ የተጣለበትን ሀላፊነት እንዳልተወጣ የሚያመለክት ግልጽ ማሳያ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት በግብርና ስራ ዘርፍ በተሰማሩ ዜጎች ላይ የሚፈጽመውን እንዲህ አይነቱን ሰብአዊ መብታቸውን የሚጥስ ተግባር በአስቸኳይ የሚያስቆም ተገቢ እርምጃ እንዲወስድ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ለሰብአዊ መብቶች መከበርና መጠበቅ የቆማችሁ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ የመንግስታትና የአለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች ለኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናትና እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ከዚህ በታች ስማቸው ለተዘረዘረው የመንግስት አካላት ሁሉ ደብዳቤ በመጻፍ መንግስት የሰብአዊ መብት ጥሰት ለደረሰባቸው አርሶ አደሮች ተገቢውን ህጋዊ ጥበቃና ካሳ እንዲሰጥ እንድታደርጉ ይጠይቃል፡፡

<u>በተለይም</u>፣

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባኤ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0900 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0722 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 1031፣ፋክስ (251-11)155 2020 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

